**Kinijit North America Association of Support Organizations (KNAASO)**

**766 Rock Creek Church Rd., NW. Washington DC, 20010**
**Tel: 202-541-0556 Fax: 202-541-0557 E-mail: kinijitna@kinijitna.org**
**www.kinijitna.org**

ታህሳስ 17 ቀን፣ 2000 ዓ.ም

# ከቅንጅት ሰሜን አሜሪካ የድጋፍ ድርጅቶች ማህበር የተሰጠ ጋዜጣዊ መግለጫ

## ቅንጅት ተጠናክሮ ይቀጥላል

በኢትዮጵያ የሚካሄደው ህዝባዊ ትግል በህዝባችን ፍላጎት ላይ የተመሰረተ በመሆኑ ከኢትዮጵያ ህዝብ ጎን በመሆን በትግሉ የመካፈል የሞራል ግዴታ እንዳለብን እናምናለን:: ማንኛውም የፖለቲካ እንቅስቃሴ በመሰረታዊ እምነቱና በፕሮግራሙ አስፍሮ በተለመው መስመር ሊያስገኛቸው ባቀዳቸው የፖሊሲ አቅጣጫዎች ይመዘናል:: በሰሜን አሜሪካ የምንገኝ የቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፓርቲ የድጋፍ ድርጅቶች፣ መሰረታዊ በሆኑ ሃገራዊ የፖለቲካ ጉዳዮች ላይ ቅንጅት ያስቀመጣቸውን አማራጫች ለሃገራችን ጠቃሚዎች ናቸው ብለን እናምናለን:: ይህም ብቻ አይደለም፣ ቅንጅት ያሰፈራቸው መሰረታዊ እሴቶች፣ የፖሊሲ አቅጣጫውን ለመቀየስም ሆነ ለማስፈጸም የሚጠቀምባቸው በመሆናቸው በፓርቲው ላይ ያለንን እምነት የበለጠ ያጠናክሩታል::

እንግዲህ ከቅንጅት ጋር አብዛኛው ኢትዮጵያዊም ይሁን እኛ የሰሜን አሜሪካ የድጋፍ ድርጅት አባላት ያለን የትስስር ሰንሰለት ምንጭ፣ ቅንጅት ያስቀመጣቸው መሰረታዊ እምነቶችና የፖሊሲ አቅጣጫዎች እንጅ ጠባብ የቡድን ስሜት ወይም የግለሰብ ትስስርና ፍቅር አይደለም:: ይህም በመሆኑ ባሁኑ ጊዜ በድርጅቱ ውስጥ የተከሰተውን ችግር አገናዝቦ ድርጅታዊ መፍትሄ ለማስገኘት የሚደረገው ጥረት ላይ ምንም ሊያሻማ የሚችል የአመለካከት ችግር አይገጥመንም::

ከመሪዎቻችን መፈታት ጋር ተያይዞ ትግሉ ወደተጠናከረና ወደተሻለ ደረጃ እንዲሸጋገርና የዲሞክራሲያዊ ስርአት ግንባታ ምስረታ እንዲፋጠን ተስፋችንና እምነታችን ጠንካራ ነው:: ይህንን ተስፋ ሊያደበዝዙ የሚችሉ ክስተቶች በቅንጅት ዙሪያ በመከሰታቸው የተሰማን ቅሬታ ከፍተኛ ነው:: በፖለቲካ ፓርቲ ውስጥ ችግሮች መከሰታቸው ድንገተኛ አደጋ ሳይሆን ሊከሰት የሚችል የእድገት ውጤት መሆኑን እንገነዘባለን:: ይህ በመሆኑም ፓርቲው ከስህተቶቹ ተምሮ ከቅንጅት እምነት መስመር ውጭ የሚንቀሳቀሱ ግለሰቦች አቋማቸውን አስተካክለው፣ የድርጅቱ ህግና ደንብ ተከብሮ፣ የበለጠ ጥራት ያለው ጠንካራ ድርጅት ሆኖ እንደሚቀጥል ምንም ጥርጥር የለንም::

የኢትዮጵያ ህዝብ ተስፋ የጣለበት ፓርቲ ተጠናክሮ አደራውን እንዲወጣ ሁሉም የበኩሉን አስተዋጽኦ ማድረግ ይጠበቅበታል:: በተለይም ጉዳዩ የሚመለከታቸው የቅንጅት አመራር አባላት በግል እራሳቸውን ከታሪክ ተወቃሽነት ለማዳን የሚችሉት ይህን ጉዳይ በሚመለከት ማድረግ የሚገባቸውን ሁሉ ለመፈጸም ሲችሉ ብቻ ነው:: በዚህ መሰረት ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን መልእክቶች ማስተላለፍ እንወዳለን::

1. የቅንጅት አመራር ህገደንቡ በሚያዘው መሰረት የስራ አስፈጻሚ አባላት ስብሰባ ለማድረግ ወደ ፓርቲው ጽ/ቤት ሲሄዱ እንዳይገቡ የተደረገው ክልከላ ፍጹም

ህገወጥና የሚያሳዝን ሆኖሳለ በቀጣዩ የላእላይ ምክር ቤት ስብሰባ ለማካሄድ የሄዱ አባላትም እንዳይገቡ መከልከል ብቻ ሳይሆን፣ ቅንጅት የሚባል ድርጅት የለም ይህ የመኢአድ ጽ/ቤት ነው በማለት የበርካታ ኢትጵያንንና በተለይም በቅንጅት መርህ ተመስርተው ጠንካራ የህዝብ ድጋፍ ያላቸውን የቀድሞ የመኢአድ አባላት የነበሩ ግለሰቦችን ልብ የሰበረ ድርጊት ተፈጽሟል፡፡በዚህ ድረጊት ዙሪያ እጃቸውን ያስገቡ ሁሉ ከዚህ አሳዛኝ ተግባራቸው እንዲገቱ እናሳስባለን፡፡

2. በድርጅቱ ውስጥ የተከሰተው ችግር ሊፈታ የሚችለው የድርጅቱን ህገደንብ ተከትሎ መሆኑን እናምናለን፡፡ ይህን ችግር በዚህ መልክ ለመፍታት ጥረት ለሚያደርጉ አመራር አባላት ያለንን አክብሮት እየገለጽን፣ የላእላይ ምክር ቤት አባላትም በዚህ ታሪካዊ ስብሰባ ላይ በመገኘት ፓርቲው ተጠናክሮ የሚወጣበትን መንገድ እንዲያመቻቹ በዚህም ታሪካዊ ግዴታቸውን እንዲወጡ ለማሳሰብ እንወዳለን፡፡

3. በቅንጅት ውስጥ የተፈጠረው ችግር ሊፈታ የሚችለው በአገር ውስጥ በድርጅቱ አመራር አባለት አማካኝነት በሚደረግ ውይይት መሆን እንዳለበት በተደጋጋሚ በሁሉም ወገን ተገልጽዋል፡፡ የድርጅቱ ሊቀመንበር አቶ ሃይሉ ሻውል በቦታው በመገኘት ታሪካዊ ግዴታቸውን መወጣት ይኖርባቸዋል ብለን እናምናለን፡፡ አንዳንድ የድርጅቱን ከፍተኛ አመራር አባላት ለማገድ ያስተላለፉት መልክት ከድርጅቱ ህገደንብ ውጭ ተደረገ ከመሆኑም ባሻገር ድርጅቱን የውስጥ ጉዳይ የበለጠ ውስብስብ ያደርገዋል፡፡ በተለይም የሳቸውን ትእዛዝ እናስፈጽማለን በሚል የቀድሞ የመኢአድ አመራር አባላት የነበሩ የሚያካሂዱትን ህገወጥ እንቅስቃሴ ዝም ብለው መመልከታቸው የሚያሳዝን ከመሆኑም በላይ በታሪክ ተወቃሽ ያደርጋቸዋል የሚል እምነት አለን፡፡ ይህም በመሆኑ ወደ አገር ቤት በመመለስ በተጠራው የላእላይ ምክር ቤት ስብሰባ ላይ በመገኘት ለጉዳዩ መፍትሄ ለማስገኘ ት ጥረት እንዲደረጉ ልባዊ መልእክት እናስተላልፋለን፡፡

4. የቅንጅት ሰሜን አሜሪካ ድጋፍ ድርጅቶች ማህበር በደርጅቱ ውስጥ የተፈጠረው ችግር አምባገነናዊ ወይም ቡድናዊ በሆነ መልኩ ሳይሆን የድርጅቱን ህገ ደንብ መሰረት ባደረገ ስልጡን መንገድ ለመፍታት የሚደረገውን ጥረት ከልብ የሚደግፍና የቅንጅትን መርህ ተከትለው ለሚጓዙ የፓርቲው አመራር አባላት ያልተቆጠበ ድጋፍ እንደሚያደረግ በዚህ አጋጣሚ መግለጥ እንወዳለን፡፡

**ቅንጅት ጠንካራ ሆኖ ይቀጥላል!**